# የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት መርሃ ግብር

## ይዘቶች


**1 አገላለጽና ትርጓሜዎች 1**

1.1 አገላለጾች 1

**2 የመፍትሄ ምስገኛ ገንዘብ አከፋፈል 5**

2.1 የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት መርሃ ግብር አስተዳደር 5

2.2 የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት መርሃ ግብር ስለመጀመር 5

2.3 ተግባር፣ ግዴታና የአስተዳዳሪዊ ስራ ድርሻ 5

2.4 ማረሚያ 5

2.5 ለአስተዳዳሪ ወጪዎች 5

**3 የቡድን አባላት ማረጋገጫና ምዝገባ 5**

3.1 ማረጋገጫ 5

3.2 የቡድን አባላት መዝገብ 6

3.3 መጠነኛ እና በአካለ ስንኩል ስር ላሉ ሰዎች 7

**4 የቡድን አባላት ግዴታዎች 7**

**5 የመጀመሪያ ማሳሰቢያ ለቡድን አባላት 8**

**6 እንደገና ግምገማ ክለሳ 8**

6.1 እንደገና እንዲታይ ክለሳ የመፈለግ መብት 8

6.2 ለግምገማ ክለሳ ለመፈለግ አሰራር ሂደት 8

6.3 ለግምገማ ክለሳ እንዲደረግ አለመፈለግ 9

6.4 ለግምገማ ክለሳዎች አሰራር ሂደት 9

6.5 በገለልተኛ ነጻ ግምገማ ክለሳ ውሳኔ የመጨረሻና አስገዳጅ ይሆናል 9

**7 ወደ ጥያቄ ማቅረቢያ ባር 9**

**8 እያንዳንዱ ብቃት ያለው የቡድን አባል ክፍያዎች ስሌት 10**

**9 የግምገማ ማስተዋወቂያ 10**

**10 ከመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ መጠን ክፍያ 10**

10.1 የከሳሾች ተመላሽ ገንዘብ 10

10.2 የቡድን አባል ክፍያዎች 10

**11 ለመፍትሄ ማስገኛ ክፍያ ማስታወቂያ 10**

**12 ማስታወቂያዎች 11**

**13 ሰዓት 11**

**14 የአስተዳደሪነት ማጠቃለያ 11**

14.1 የማከፋፈያ ስርጭት ሪፖርት 11

14.2 የአስተዳዳር መጨረሻ 12

**15 ትርጉም 12**

# አመጣጥ ታሪክ

A ከሳሽና ተከሳሽ የመፍትሄ እርቅ ውሉን ፈጽመዋል።

B ይህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሐ ግብር በመፍትሄ ስምምነት ውሉ መሰረት እና ፍርድ ቤቱ በፈቀደው መሰረት የሚከፈልበትን የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ የመከፋፈልና የአከፋፈል አሰራር ሂደት ይደነግጋል።

C በፍርድ ቤቱ የጸደቀው ትእዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ይህ የመፍትሄ እርቅ ገንዘብ ስርጭት ዘዴ አይሠራም።

D ይህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር የሚከተሉትን ደረጃዎች እንዲፈጸሙ ከሌሎች ነገሮች ጋር በተጨማሪ ያቀርባል።

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፕሮፌሰር ዩዋን ዋላስ አሜ/ Professor Euan Wallace AM የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት መርሃ ግብር አስተዳዳሪ ሆነው እንደተሾሙ ነው።

አስተዳዳሪው የቡድን አባላት መዝገብ ይፈጥራል, ብቃት ያላቸውን የቡድን አባላት ይዘረዝራሉ።

አስተዳዳሪው የመጀመሪያ ማስታወቂያውን ለቡድኑ አባላት በመስጠት በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል ላይ ለመሳተፍ እንዲመዘገቡ ይጠይቃል።

አስተዳዳሪው የመልሶ ማከፋፈያ ገንዘብ ከሰፈራ ውሰጥ ለከሳሾች ይከፍላል።

አስተዳዳሪው ለእያንዳንዱ ብቃት ያለው ቡድን አባል የመፍትሄ ማስገኛ ክፍያዎችን ስሌት ያካሂዳል።

አስተዳዳሪው ለእያንዳንዱ ብቃት ያለው ቡድን አባል ያላቸውን ጥያቄ በተመለከተ የግምገማ ማስታወቂያ ይልካል።

አስተዳዳሪው የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብን ለእያንዳንዱ ብቃት ያለው ቡድን አባል ለውዝፍ የተከፈለን ቅናሽ ካደረገ በኋላ የመፍትሄ ማስገኛ ክፍያውን ያከፋፍላል።

---

# ተግባራዊ የሥራ ክፍል

## 1 አገላለጽ እና ትርጓሜዎች

### 1.1 መግለጫዎች

በጥቅሱ ዙሪያ ያለው ሀሳብ ሌላ ነገር ካልተከተለ በስተቀር የሚከተሉት መግለጫዎች ይሠራሉ፡

| | |
|---|---|
| **ህግ አንቀጽ** | ይህ ማለት *ጠቅላይ ፍርድ ቤት አዋጅ አንቀጽ ህግ 1986* (Vic)፤ |
| **አስተዳዳሪ** | ማለት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጸሀፊ ፕሮፌሰር ዩዋን ዋላስ ኤ.ማ./ Professor Euan Wallace AM እንደሆኑ ነው። |
| **ጎልማሳ** | ይህ ማለት ሀምሌ/ July 4 ቀን 2020 ዓ.ም ስሆን እድሜው ከ16 ዓመት በላይ የሆነ ሰው ማለት ነው። |
| **ASOC** | ይህ መስከረም/September 24 ቀን 2021 ዓ.ም. የተሻሻለው ጥያቄ ማቅረቢያ ጽሁፋዊ መግለጫ ማለት ነው። |

| | |
|---|---|
| **የጸደቀ ትእዛዝ በቀን ውሎ** | ማለት በቀኑ መጨረሻ ማለት፡<br>(a) ፍርድ ቤቱ ያስተላለፈዉን ተቀባይነት ያገኘ ትእዛዝ በተመለከተ አቤቱታ የሚቀርብበት ጊዜ ያለምንም ይግባኝ ወይም የይግባኝ ማመልከቻ ሳይቀርብበት እንዳለፈ፤ እና<br>(b) ፍርድ ቤቱ ከስምምነት ትእዛዞች ይግባኝ ለመጠየቅ የጸደቀውን ትእዛዝና አቤቱታ ይግባኝ ወይም ማመልከቻ ከተጀመረ፣ የይግባኝ አቤቱታ ሰሚው ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ (ከዚያ በኋላ አቤቱታ ወይም ይግባኝ ለመጠየቅ ማመልከቻን ጨምሮ) ከሶስት የሥራ ቀናት በኋላ ይቀርባል። |
| **የጸደቀ ትእዛዝ** | ማለት በአዋጅ አንቀጽ ህግ 33V ስር የፍርድ ቤት ትእዛዞች ማለት ነው። በተሻሻለ አንቀጽ ህግ እርምት እና በመፍትሄ ማስገኛ ውሉ ውስጥ በተደነገጉት መሰረቶች ላይ ማጽደቅ፣ እንዲሁም ይህንን የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር (ወይም ፍርድ ቤቱ ያደረገውን ማናቸውንም ማሻሻያዎች የሚያካትት ይህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት መርሃ ግብር) ማጽደቅ ይሆናል። |
| **የሥራ ቀን** | ማለት ባንኮች የሚከፈቱበት ቀን ማለት ሲሆን<br>ንግድ በሜልቦርን ከተማ እና ቅዳሜ፤ እሁድ ወይም የህዝባዊ በዓልን ሳይጨምር ይሆናል። |
| **ህጻን** | ማለት እንደወንድ ልጅ ከ16 ዓመት በታች በቀን 4 ሐምሌ/July 2020። |
| **ጥያቄ አቤቱታዎች** | ማለት የከሳሾችና የቡድን አባላት ክስ ማለት በASOC የተቅናጀው መሰረት እና በመልስ ማቅረቢያ ቀን 27 ጥር/January 2022 ዓ.ም በተቀናጀው መሰረት እንዲሁም ከአሰራር ሂደት ጉዳይ ወይም ተመሳሳይ ወይም ተመሳሳይ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ወይም ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ ወይም የሚነሱ ሁሉም አቤቱታዎች ናቸው። |
| **ፍርድ ቤት** | ማለት የቪክቶሪያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው። |
| **ተከሳሽ** | ማለት የቪክቶሪያ አስተዳደር ክልል ነው። |
| **ብቃት ያለው ቡድን አባል** | ማለት ለመቀበል ብቃት ያለው የቡድን አባል ማለት ነው በዚህ የመፍትሄ ማስገኛ ግዝዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር መሰረት በአስተዳዳሪው በተሰላው መሰረት ከመፍትሄ ማስገኛ መዋቅሩ የሚከፋፈል ነው። |
| **ነመኖሪያ እርስት ህንጻዎች (Estate Towers)** | ማለት በዚህ እንደሚከተለው አድራሻዎች ይቀርባል፡<br>• 12 Holland Court, Flemington 3031;<br>• 120 Racecourse Road, Flemington 3031;<br>• 126 Racecourse Road, Flemington 3031;<br>• 130 Racecourse Road, Flemington 3031;<br>• 9 Pampas Street, North Melbourne 3051;<br>• 12 Sutton Street, North Melbourne 3051;<br>• 33 Alfred Street, North Melbourne 3051;<br>• 76 Canning Street, North Melbourne 3051;<br>• 159 Melrose Street, North Melbourne 3051። |

| | |
|---|---|
| **}ለመጀመሪያ ጊዜ (First Period)** | ማለት ወደ ከሰዓት በኋል 4.00PM ወይም 4.30PM በቀን 4 ሀምሌ/July 2020 ዓ.ም እስከ ከሰዓት በኋላ 5.00PM በቀን 9 ሀምሌ/July 2020 ዓ.ም (ምናልባት በአድራሻ፡ 9 Pampas Street; North Melbourne እና 159 Melrose Street፤ North Melbourne) እንዲሁም አካባቢ ከሰዓት በኋላ 4.00 PM ወይም ከሰዓት በኋላ 4 30PM በቀን 4 ሀምሌ/July 2020 ዓ.ም (ወይም ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ) እስከ 11 59PM ሀምሌ/July 9 ቀን 2020 ዓ.ም በሁሉም የመኖሪያ እርስት እስቴት ህንጻዎች/Estate Towers ጉዳይ። |
| **ቡድን አባል** | በ ASOC ውስጥ ያለውን መግለጫ ያላሟላ የቡድን አባልሰው ማለት ሲሆን፡ ከፕሮሲዲንግ ወደ ኋላ አልተመለሰም በአንቀጽ ህግ ቁጥር 33J መሰረት የክስ አሰራር ሂደት ሲሆን ከሳሾችንም ያካትታል። |
| **የቡድን አባል ክፍያ** | በአስተዳዳሪው የሚሰላው መጠን በ8 መሰረት እና ብቃት ላለው የቡድን አባላት የሚከፋፈልበት መጠን ማለት ነው። |
| **የመጀመሪያ ማስታወቂያ** | በአንቀጽ ህግ ክፍል 5 ላይ የተገለጸው ማስታወቂያ ማለት ነው። |
| **አነስተኛ መጠን** | ማለት በትእዛዝ ስርዓት የ15 ደንቦች ትርጉም በአነስተኛ መጠን የደረሰ የቡድን አባል ማለት ነው |
| **ስለተካሄደ ግምገማ ማሳሰቢያ** | በአንቀጽ ህግ ክፍል 11 ላይ የተገለጸው ማሳሰቢያ ማለት ነው። |
| **ለመፍትሄ ማስገኛ ክፍያ ማሳሰቢያ** | በአንቀጽ ህግ ክፍል 11 ላይ እንደተገለጸው ማስታወቂያ ማለት ነው። |
| **የአካል ጉዳተኛ የሆነ ሰው** | ማለት በአዋጅ አንቀጽ ህግ ቁጥር 33A እና በደንቡ ስርዓትቁጥር አንቀጽ ህግ 15 ደንቦች መሰረት "አካል ጉዳተኛ" የሆነ ሰው ማለት ነው። |
| **የከሳሽ ለህጋዊ ወጪዎች** | ከሳሾች በራሳቸው እና/ወይም በሁሉም የቡድን አባላት ወክለው የፈጸሙበት አግባብ ያለው የህግ ወጪ እና ክፍያ ማለት ሲሆን በፍርድ ቤቱ በጸደቀው መሰረት የመፍትሄ ስምምነት ማመልከቻን በተመለከተ የከሳሾችን ወጪ ያካተተ ነው |
| **በአሰራር ሂደት ላይ** | ማለት ሃሳን ከቪክቶሪያ አስተዳደር ክልል S ECI 2021 00826 የተደረገ ማለት ነው። |
| **ምልሶ የሚከፈል መጠን** | ይህም ማለት ከሳሾቹ ከመፍትሄ ማስገኛ ስምምነት ገንዘብ ላይ እንዲከፈላቸው እንደ ዋና ከሳሾች ያላቸውን አቋም በመገንዘብ በፍርድ ቤቱ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት የሚፈልጉት ማንኛውም መጠን ማለት ነው። |
| **የቡድን አባላት ምዝገባ** | በምዝገባ ቀን በመፍትሄ ስርጭት ለመሳተፍ የተመዘገቡ የቡድን አባላትን ያቀፈ በአስተዳዳሪ የተዘጋጀው መዝገብ ማለት ነው። |
| **የምዝገባ ቀን** | የቡድን አባላት በመፍትሄ ማስገኛ ስርጭት ላይ ለመሳተፍ ያላቸውን ፍላጎት ማስመዝገብ የሚጠበቅባቸው በቀን 27 ሰኔ/June 2023 ዓ.ም ማለት ነው። |
| **ጠቂሜታ ያለው ጊዜ** | የመጀመሪያና ሁለተኛው ጊዜ ማለት ነው። |

| | |
|---|---|
| **ደንቦች** | *ይህ ማለት ጠቅላይ ፍርድ ቤት (አጠቃላይ ፍትሃብሄር አሰራር ሂደ/General Civil Procedure) ደንቦች 2015* (Vic) |
| **የተቃውሞ መርሃ ግብር** | ይህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር በአጠቃላይ የቡድን አባላትን ጥቅም እና በተለይም በመካከላቸው ሚዛናዊነትን ለማስጠበቅ በማሰብ የማስተዳደር ዓላማ ማለት ነው: <br>(a) በተቻለ መጠን ብዙ ብቃት ላላቸው የቡድን አባላት በዚህ የመፍትሄር ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር መሰረት የመፍትሄር ማስገኛን ክፍያ ለመቀበል የሚያስችል ጊዜና እድል መስጠት፤ <br>(b) ፡ይህን የመፍትሄር ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር ተግባራዊ በማድረግ ላይ የሚገኘው የአስተዳደር ወጪ ምክንያታዊ እና ይህን የመፍትሄር ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች እንደ አጠቃላይ የቡድን አባላትን ፍላጎት ግምት ውስጥ በመጣል ተግባራዊ፤ ተመጣጣኝ እና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆኑ ማድረግ እና <br>(c) በተመጣጣኝ ጊዜ ውስጥ በብቁነት ፈቃድ ላላቸው ቡድን አባላት የመፍትሄ ማስገኛ ክፍያ ማቅረብ። |
| **የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት መርሃ ግብር** | ማናቸውንም ፕሮግራሞች እና ማጣቀሻዎች ጨምሮ በፍርድ ቤቱ በጸደቀው መሰረት ይህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት መርሃ ግብር መሰረት ያደረገ ማለት ነው። |
| **ሁለተኛ ጊዜ** | ማለት ሀምሌ/July 9 ቀን 2020 ዓ.ም ከምሽቱ 11 59 ሰዓት ጀምሮ እስከ 11 59 pm በቀን 18 ሀምሌ/July 2020 ዓ.ም ማለት ነው። |
| **የመፍትሄ ስምምነት ውል** | በቡድን/ፓርቲዎች የተፈጸመው የመፍትሄ እርቅ ውል ማለት ነው። መጋቢት/March 3 ቀን 2023 ዓ.ም። |
| **የመፍትሄ ማስገኛ ጠቅላላ ገንዘብ** | ይህም ማለት ለወለድና ለተመልሶ የተከፈለ ገንዘብ እንዲሁም ህጋዊ ወጪዎችንና የገንዘብ ወጪዎችን ሳይጨምር ማንኛውንም ገንዘብ ጨምሮ የAUD $5,000,000.00 ዶላር ማለት ነው። |
| **ክፍል/ዩኒት** | ከመፍትሄ ማስገኛ ጠቅላላ ገንዘብ መጠን ውስጥ ስምሪት ክፍል አንድ ብቃት ያለው ቡድን አባል በአንቀጽ ህግ 8 በተደነገገው መሰረት የመቀበል መብት አለው። |

# 2 የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል

## 2.1 የመፍትሄ ማስገኛ ስርጭት መርሃ ግብር አስተዳደር

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፕሮፌሰር ዩዋን ዋላስ/ Professor Euan Wallace, AM የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል አስተዳዳሪ ነው።

## 2.2 የመፍትሄ ማስገኛ ስርጭት መርሃ አጀማመር

የመፍትሄ ማስገኛ ስርጭት መርሃ ግብር የሚጀምረው ፍርድ ቤቱ ያጸደቀውን ትእዛዝ በሚሰጥበት ቀን ነው።

## 2.3 የአስተዳዳሪው ሥራ ድርሻ፣ ግዴታና ሚና

(a) በዚህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር ውስጥ የተገለጸውን የአስተዳዳሪውን ሥራ ድርሻዎች፣ ግዴታዎችና ሚና ሳይገደብ አስተዳዳሪው፡

- (i) በዚህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ መርሃ ግብርና በመርሃ ግብሩ ዓላማ መሰረት የሰፈራውን ገንዘብ ማስተዳደርና ማከፋፈል አለበት፤
- (ii) በዚህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ መርሃ ግብር፣ በመርሃ ግብር ዓላማ እና በፍርድ ቤቱ በተሰጠው ማናቸውም ትእዛዝ መሰረት በተቻለ መጠን በፍጥነት ተግባራዊ መሆን አለበት፤
- (iii) ግዴታዎቹን በህሊና፣ በጥሩ እምነት፣ በተገቢው ጥንቃቄና ችሎታ እንዲሁም በቡድን አባላት በአጠቃላይ በሚጠቅም እንጂ ለየትኛውም የቡድን አባል ተወካይ በመሆን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መወጣት አለበት፤
- (iv) የሶስተኛ ወገን አገልግሎት ሰጪዎችን፣ ጠበቆችን፣ የግብር አማካሪዎችን፣ የምዝገባ አገልግሎት ሰጪዎችን እና የመላኪያ ቤቶችን ጨምሮ ማሳተፍ ይችላል፤

## 2.4 እርምት

አስተዳዳሪው በማንኛውም ጊዜ በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል አሰራር ፕሮግራም በአስተዳደራቸው ውስጥ የለሚከሰተው ማንኛውንም ስህተት፣ መሳሳት ወይም ማጥፋት ሊያስተካክል ይችላል።

## 2.5 የአስተዳዳሪ ወጪዎች

የአስተዳዳሪው ወጪ ከመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ውሰጥ እንደማይቀነስ እና በተከሳሹ ይከፈለዋል።

# 3 የቡድን አባላት ማረጋገጫ እና ምዝገባ

## 3.1 ማንነትን ማረጋገጫ

(a) አስተዳዳሪው የእያንዳንዱ ቡድን አባል ማንነትና ብቃት እንዲሁም እድሜ ለማረጋገጥ ሁሉንም ምክንያታዊ የሆኑ እርምጃዎች መወሰድ ያለበት በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት ላይ ለመሳተፍ፤

- (i) የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብን ለማከፋፈል (እንደ ስም፣ፆታ፣የልደት ቀንና አድራሻ የመሳሰሉት) በማጣራት በገንዘብ ስርጭት ላይ ለመሳተፍ የተመዘገቡ የእያንዳንዱን ቡድን አባል ማንነት ማረጋገጥ ለአስተዳዳሪው ካለዉ መረጃ ጋር ይጣጣማል፤
- (ii) ይህም ማንነት መለያቸውን ለማረጋገጥ የቡድን አባላትን በስልክ፣ በኢሜል፣ በማህበራዊ ሚዲያ ወይም በሌላ መንገድ ማነጋገር፤
- (iii) የቡድን አባላት ማንነታቸውን ለማረጋገጥ እና በመኖሪያ እርስት እስቴት ህንጻዎች ውስጥ መኖራቸውን ወይም እዚያው የቆዩትን (ወይም በአካል ጉዳተኝነት ወቅት፣ ህጋዊ ሞግዚቶቻቸውን ወይም የግል ተወካዮቻቸውን እንዲህ ያለውን ስሁፋዊ ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ መጠየቅ) እና/ወይም ማንኛውም ሌላ መረጃ ወይም ሰነድ ማንነታቸውንና በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት ላይ ለመሳተፍ ያላቸውን ብቃት ለማረጋገጥ፣ እና
- (iv) የቡድን አባላት ወይም ሌሎች ሰዎች ተያያዥ መረጃዎችን ለማግኘት በቃለ መጠይቅ ላይ እንዲገኙ መጋበዝን ጨምሮ የአንድ ቡድን አባል በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል ስርጭት ላይ ለመሳተፍ የሚያስችል ማንነት እና ብቃት ለማረጋገጥ ማንኛውንም ሌላ ምክንያታዊ ጥያቄዎች ማቅረብ ይሆናል።

(b) አስተዳዳሪው የአንድን ቡድን አባል ማንነትና የብቃት ፈቃድን ለማረጋገጥ ምን ዓይነት እርምጃዎች ተገቢ እንደሆኑ ሊወስን ይችላል።

(c) አስተዳዳሪው የቡድን አባል መለያ ወይም በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት ላይ ለመሳተፍ የሚያስችል የብቃት ፈቃድን ማረጋገጥ እንደማይቻል ከገለጸ፣ አስተዳዳሪው አንድ የቡድን አባል ምዝገባ በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል ላይ ለመሳተፍ መወሰኑ ከንቱ እና ምንም ውጤት የሌለው እንደሆነ ሊወስን ይችላል።

## 3.2 የቡድን አባላት ምዝገባ

(a) ፍርድ ቤቱ ያጸደቀውን ትእዛዝ ካዋለ በኋላ በተቻለ ፍጥነት ተግባራዊ እንዲሆን፤ አስተዳዳሪው የቡድን አባላት መዝገብ ማዘጋጀት አለበት።

(b) አስተዳዳሪው ማድረግ ያለበት:

(i) የቡድን አባላት መዝገብ መያዝ፤

(ii) ለቡድን አባላት የሚላኩ ማስታወቂያዎች ምክንያት፤

(iii) እያንዳንዱ የቡድን አባል የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል ላይ ለመሳተፍ ያላቸውን ጥያቄ ይገመግማሉ፤

(iv) የቡድን አባል ክፍያ ለብቁ ፈቃድ ላላቸው ቡድን አባላት እንዲከፈል በማድረግ፤ እና

(v) የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭቱን ሲጨርሱ፣ ስለተደረገው የቡድን አባል ክፍያ የሚገልጽ ስና መላው የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ መሚሚቱን የሚያረጋግጥ ሪፖርት ለፍርድ ቤቱ ይቀርባል።

(c) ቡድን ፓርቲዎቹ የሚከተሉትን መረጃዎች እስካላቸው ድረስ ፍርድ ቤቱ ያጸደቀውን ትእዛዝ ከተሰጠ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለአስተዳዳሪው ማቅረብ አለባቸው:

(i) በአሰራር ሂደት ውስጥ የቀረቡ የውጪ ማሳሳሰቢያ ቅጅዎች፤ እና

(ii) የቡድን አባላት ሊሆኑ ለሚችሉ በመጨረሻ ለታወቁ የመኖሪያ አድራሻዎች ይሆናል።

(d) አስተዳዳሪው እንደ የጸደቀው ትእዛዝ ቀን መሰረት የመውጫ ማስታወቂያ ያስገቡትን እና በቡድን አባላት መዝገብ ውስጥ ወደ አሰራር ሂደቱ ለመመለስ ላልተመለሱ ግለሰቦችን ማካተት የለበትም።

(e) የቡድን አባላት መዝገብ የሚከተሉትን ጨምሮ ከእያንዳንዱ ብቃት ያለው ቡድን አባል ጋር በተያያዘ መረጃ ለመያዝ:

(i) ስም፤

(ii) የሚከተለውን ያካተተ ዝርዝር አድራሻ:

(A) የአሁን መኖሪያ አድራሻ፤

(B) ስልክ ቁጥር፤ እና

(C) ኢሜል አድራሻ።

(iii) የልደት ቀን፤

(iv) የቡድን አባል ከዚህ ጋር በተዛመደ በወቅቱ የነበረበት ወይም የኀበኘበት የመኖሪያ ህንጻዎች አድራሻ፤

(v) የቡድን አባል በዚህ ጠቃሚ በሆነበት ወቅት የመኖሪያ እርስት እስቴት ህንጻዎች ነዋሪ ወይም ኀብኚ መሆን፤

(vi) የቡድን አባል በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል ላይ ይሳተፋል የሚለውን ጥያቄ ለይቶ ለማወቅና ማስረጃ ለማቅረብ የቀረቡ ማስረጃዎች አንድ ቅጂ ሊያካትት ቢችልም የተወሰነ እንዳልሆነ:

(A) የመኖሪያ ቤት ኪራይ ኩንትራት(s) በዚህ ተያያዥነት ያለውን ጊዜ ያካትታል፤

(B) የስልክ፣ የኤሌክትሪክ ሃይል፣ ኢንተርኔት፣ የጋዝ ሂሳብ ወይም የባንክ ሂሳብ ከዚህ ጠቃሚ ጊዜ ጋር የተያያዘ፤

(C) በዚህን ጠቃሚ ወቅት የተጻፉ የህክምና ደብዳቤዎች ወይም ሰነዶች፤

(D) ሴንተርሊንክ ደብዳቤ እና ማስታወቂያዎች፤

(E) የመንጃ ፈቃድ ወይም ቅጂ የመንጃ ፈቃድ ወይም የለማጅ መንጃ ፈቃድ ኮፒ፤

(F) የቡድን አባልን ብቃት ፈቃድ ለማረጋገጥ እና በመኖሪያ እርስት እስቴት ህንጻዎች ውስጥ ማንነታቸውን፣ እድሜያቸውንና አድራሻቸውን ለማረጋገጥ የተጠቀሙበት መዝገቦች፤ እና/ወይም

(G) አግባብ ያለው የቡድን አባል በሁሉም ወይም በተወሰኑ ጊዜ ውስጥ በመኖሪያ እርስት እስቴት ህንጻዎች ነዋሪ ወይም ጎብኚ መሆኑን በጽሁፍ ህጋዊ የሆነ ምስክርነት ይሆናል።

## 3.3 ለአካለ መጠን ያልደረሱና አካለ ስንኩል የሆኑ ሰዎች

(a) አስተዳዳሪው ምክንያታዊ በሆነ መንገድ አንድ የቡድን አባል አካል ጉዳተኛ የሆነ ሰው እንደሆነ ወይም ሊሆን እንደሚችል ካመነበት (ለአካለ መጠን ያልደረሰን ቃል የሚያካትት)፡

(i) አስተዳዳሪው ጽሑፋዊ ማሳሰቢያ ለቡድን አባል ማሳወቂያ ሊሰጥ ይችላል;

(ii) አስተዳዳሪው ይህን እምነት ለማረጋገጥ ለቡድን አባል በጽሁፍ ማሳሰቢያ ሊሰጥ ይችላል፤ የቡድን አባል የግል ተወካያቸውን ሰው መሾም ይችላሉ። እንዲሁም በህግ አንቀጽ 3.3(ለ) መሰረት አስተዳዳሪው ያንን ግለሰብ የቡድን አባል የግል ተወካይ አድርጎ መሾም እንዳለበት፤ እና

(iii) በንዑስ አንቀጽ ህግ 3.1(ii) ጋር በተመሰረተ ማንኛውም የምረጫ ፈቃድ ባለመኖሩ፣ አስተዳዳሪው ከመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር አሠራር ጋር በተያያዘ ለዚያ ቡድን አባል የግል ተወካይ መሾም አለበት።

(b) የአካል ጉዳተኞች ቡድን አባል ፍላጎት በሚጠይቀው ቦታ አስተዳዳሪው ማድረግ የሚችለው፡

(i) የዚያ ቡድን አባል የግል ተወካይ መሾም ወይም ማስወገድ፤ ወይም

(ii) የዚያ ቡድን አባል የግል ተወካይ በሌላ ሰው መተካት።

(c) አስተዳዳሪው በቡድን አባል ጥያቄ መሰረት ለዚያ ቡድን አባል የግል ተወካይ አድርጎ ሊሾም ይችላል። ምንም እንኳን የቡድን አባል ባይሆንም፣ አስተዳዳሪውም ቢሆኑ በአካል ጉዳተኝነት ስር ያሉትን ሰዎች ምክንያቱ ምን እንደሆነ አይረዳም። አስተዳዳሪው በዚህ አንቀጽ መሰረት የቡድን አባል የግል ተወካይ ሆነው መሾማቸውን ለግለሰቡ በጽሑፍ አድርጎ ማሳወቅ አለበት።

(d) አንድ የግል ተወካይ የሚሾመው በአንቀጽ ህግ 3.3(ሀ)፣ 3.3(ለ) እና 3.3(ሐ) በሚሉት መሰረት ከሆነ የዚህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር አሰራር በሚከተለው መልኩ ይስተካከላል፡

(i) በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር ወይም በአስተዳዳሪው ካልተሰጠ በስተቀር፣ በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር ወይም በአስተዳዳሪው የሚፈለግ ማንኛውም ነገር በጋራ ቡድን አባል (ለግምገማ ማመልከቻ ማቅረብን ጨምሮ) በግል ተወካዩ መደረግ እንዳለበት፤ እና

(ii) ከቀጠሮው ቀን በኋላ የሚወጡ ማናቸውም ማስታወቂያዎች፣ ደብዳቤዎች ወይም መረጃዎች ለዚያ ቡድን አባል የግል ተወካይ መሰጠት አለበት።

(e) አንድ የግል ተወካይ በሚሾምበት ጊዜ በአንቀጽ ህግ 3.3(ሀ) እና 3.3(ለ) በተደነገገው መሰረት የሚሾም ከሆነ የዚህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር አሠራር በዚህ መሰረት ማስተካከያ መደረግ አለበት። በፍርድ ቤቱ የተሰጠ ተጨማሪ ትእዛዝ መሰረት ለዚሁ ቡድን አባል የሚደረግ ማንኛውም ክፍያ የቡድን አባልን ወክሎ ለግል ተወካዩ ይከፈለዋል።

(f) ለአካለ መጠን ያልደረሰ ወይም አካለ ስንኩል የሆነ ግለሰብ ወላጅ ወይም ሞግዚት ወይም የአካል ጉዳተኛ ለሆነ ግለሰብ የግል ተወካይ የሆኑላቸውን የአካል ጉዳተኞች ወኪል ወክለው ለዚህ የስምምነት ስርጭት መርሃ ግብር የሚያስፈልገውን የጥያቂ መግለጫ እና ማንኛውም ሌላ ሰነድ ማጠናቀቅና መመለስ ይችላሉ።

# 4 የቡድን አባላት ግዴታ

(a) በዚህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር ማንኛውም የቡድን አባል ከአስተዳዳሪው ወይም ከመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ምንም ዓይነት ህጋዊ ወጪ ወይም የመሳሰሉ ወጪዎች እንዳይጠየቁ በራሱ ወጪ ህጋዊ ወኪል ሆኖ እንዳይቀጥል የሚያግደው ምንም ነገር የለም።

(b) እያንዳንዱ የቡድን አባል በዚህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር ውስጥ የተደነገጉትን ነገሮች በሙሉ ወይም በአስተዳዳሪው በምክንያታዊ ነት እንደተጠየቀ ወይም እንደተመራ ማድረግ አለበት፤ በዚህ የሚካተት፡

(i) የባንክ ዝርዝሮችን ጨምሮ መመሪያዎችን፣ መረጃዎችን ወይም ሰነዶችን ማቅረብ፤

(ii) በአስተዳደሪው በምክንያታዊነት አስፈላጊ እንደሆነ የሚታሰብ ስልጣናትን ወይም ፍቃዶችን በመስጠት የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብርን ተግባራዊ ማድረግ፤ እና

(iii) አስተዳዳሪው ወይም ፍርድ ቤቱ የወሰነውን ማንኛውንም የጊዜ ገደብ ማክበር።

(c) አንድ የቡድን አባል በዚህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት መርሃ ግብር ውስጥ የተደነገጉትን ነገሮች ወይም በአስተዳዳሪው ወይም በፍርድ ቤቱ የተጠየቀውን ወይም በመመሪያው መሠረት በአስተዳዳሪው ወይም በፍርድ ቤቱ የተደነገገውን ማንኛውንም ምክንያታዊ የጊዜ ገደብ ማክበርን ጨምሮ የማያደርግ ከሆነ፣ አስተዳዳሪው የቡድን አባል በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት ውጤት ላይ ለመሳተፍ ብቃት እንደሌለው ሊያስብ ይችላል።

(d) እያንዳንዱ የቡድን አባል እንዲህ ያለ ለውጥ ከተከሰተ በኋላ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በአድራሻቸው ዝርዝር ወይም በባንክ ሂሳብ ዝርዝር ውስጥ ማንኛውንም ለውጥ ለአስተዳዳሪው ማሳወቅ አለበት።

# 5 የመጀመሪያ ማስታወቂያ ለቡድን አባላት

(a) በተቻለ ፍጥነት ተግባራዊ እንዲሆን አስተዳዳሪው ያንን የመጀመሪያ ማስታወቂያ ወደ ቡድን አባላት መላክ አለበት፤ ቢያንስ ለሚከተሉት ያካተተ፡

(i) ለአቤቱታ ጥያቄ ያቀረበ ግለሰብ ብቃት ያለው ቡድን አባል ተደርጎ ይወሰድ እንደሆነና እንዳልሆነ በአስተዳዳሪው ቁርጠኛነት ሲሆን፤ እንዲሁም፤

(ii) ብቃት ያለው ቡድን አባል ተደርጎ ከተገለጸ፡

(A) ለአካለ መጠን የደረሱ ወይም ህጻን ቢሆኑም በአንቀጽ ህግ 8 መሰረት ለአላማ ይመደባሉ፤

(B) በአቤቱታ ጥያቄ ማቅረቢያ ላይ አስቀድሞ ያልቀረበውን፣ የብቃት ቡድኑ አባል ክፍያ ለማድረግ ሲባል የባንክ ሂሳብ ዝርዝር ለማቅረብ ጥያቄ ማቅረብ፣ እና

(iii) ተጨማሪ መረጃ የሚያስፈልግ ከሆነ እንደ አስተዳዳሪው እንደዚህ ዓይነት ማስረጃ፣ ማረጋገጫ ወይም መረጃ ለማቅረብ ጥያቄ ማቅረብ፣ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ መጠን ስምሪት ስርጭት ላይ ለመሳተፍ የቡድን አባላት ማንነት፣ እድሜና ብቃት ማረጋገጫ እንዲረዳ ለማድረግ፤

(iv) በመጀመሪያ አንቀጽ ህግ 6መሰረት የአስተዳዳሪውን ውሳኔ የመከለስ መብትን በተመለከተ የተሰጠ ማብራሪያ፤

(v) የቡድን አባል ያለውን ጉዳይ እንደገና የመከለስ መብቱን ለመጠቀም የሚያስችል ዘዴ ማለት እንደሆነ፤ እና

(vi) በአስተዳዳሪው የተሰጠን ቁርጠኝነት እንደገና መገምገም አለበት፤ የቡድን አባልን ጥያቄ በመወሰነው አስተዳዳሪው ላይ የተመሰረተውን ጽሑፍ ወደ ተጽእኖ ለሌለው እንደገና ግምገማ እንዲደረግ መስማማት።

# 6 እንደገና ግምገማ

## 6.1 እንደገና ግምገማ እንዲደረግ የመፈለግ መብት

(a) ከአንቀጽ ህግ 6.2 ጋር በተደነገገው መሠረት አንድ የቡድን አባል ስለመሆን አለመሆኑን በተመለከተ በአስተዳዳሪው የተሰጠ ውሳኔ ላይ እንደገና ግምገማ እንዲደረግ ሊጠይቅ ይችላል፡

(i) በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት ላይ የመሳተፍ መብት ያለው ብቃት ፈቃድ ያለው ቡድን አባል፤ ወይም

(ii) ለአካለ መጠን የደረሰ ወይም ልጅ ተብሎ የሚመደበው በአንቀጽ ህግ 8(a)(ii)

መሰረት ነው።

**(ገምጋሚ)።**

(b) አንድ የቡድን አባል በዚህ የመፍትሄ ገንዘብ ስርጭት መርሃ ግብር መሰረት አስተዳዳሪው ያደረገውን ማንኛውንም ሌላ ውሳኔ በራሱ የመከለስ መብት የለውም።

## 6.2 ለእንደገና ግምገማ ስለመፈለግ ሂደት

አንድ የቡድን አባል እንደገና ግምገማ እንዲደረግ ከፈለገ የግድ ስለሆነ፤ እነሱ፡

(a) ለቡድን አባል የተላከው የመጀመሪያ ማስታወቂያ ከተላከበት ከ10 የሥር ቀናት በኋላ ለአስተዳዳሪው ጽሁፋዊ ማሳሰቢያ መስጠት፤

(b) ይህም ምክንያቱን (ቶችን) የቡድን አባል በአስተዳዳሪው ውሳኔ ላይ የሚከራከርበትን እና የድጋፍ ሰነድን የሚያቀርብበትን ምክንያት እንደሚገልጽ፤ እና

(c) በአንቀጽ ህግ 6.4(c) ላይ የተጠቀሱትን ነገሮች አስተዳዳሪው ለተጽእኖ የሌለበት ብቸኛ እንደገና ገምጋሚ እንዲሰጥ ስምምነት።

## 6.3 እንደገና ግምገማ ክለሳ ለማድረግ አለመቻል

አንድ የቡድን አባል አባል የመጀመሪያ ማስታወቂያ ከላኩ በኋላ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ የቡድን አባል ክፍያ ክለሳ እንዲደረግ ለአስተዳዳሪው የጽሁፍ ማሳሰቢያ ካላቀረበ፤ አስተዳዳሪው በግምገማ ማስታወቂያ ውስጥ ያለው ውሳኔ የመጨረሻ አድርጎ እና ምንም እንደገና ክለሳ ሊፈለግ እንደማይችል ነው።

## 6.4 ለግምገማ ክለሳዎች አሰራር ሂደት

አስተዳዳሪው በሚከተለው አሰራር መሰረት ክለሳዎችን በመገምገም ይወስናል፡

(a) በመጀመሪያው አሰራር ሂደት አስተዳዳሪው በአንቀጽ ህግ6.2 ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት የቀረበውን እንደገና ግምገማ ክለሳ ይመለከታል። በመጀመርያው ማስታወቂያ ላይ ያላቸውን ማንኛውንም ውሳኔ ሊያሻሽል ይችላል።

(b) አስተዳዳሪው በመጀመርያ ጥያቄ ያለን ውሳኔ ካላስተካከለ ማንኛውም እንደገና ግምገማ ክለሳ እንዲደረግ ቢያንስ የሶስት ዓመት ልምድ ላለው የቪክቶሪያ ባት አንጋፋ የህግ ጠበቃ ማመልከት አለበት። አስተዳዳሪው የዚያ ቡድን አባል በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት (**ነጻ ተስእኖ በሌለው**) ውሳኔ ላይ ለመሳተፍ በአስተዳዳሪው የመጀመሪያ ቁርጠኝነት አብሮ ያልተካፈለ ነው። ተጽእኖ በሌለበት ገምጋሚ ለመምረጥ በቡድን ፓርቲዎች መካከል በሚደረግ ስምምነትና ስምምነቱ ባለመሳካት መሆን አለበት። አስተዳዳሪው በቪክቶሪያ ህግ ባር ውስጥ ቢያንስ የሶስት ዓመት ልምድ ያላቸውን ሶስት አንጋፋ ጠበቆች አጠር ያለ ዝርዝር ተራ ለከሳሾች ያቀርባል። ከዚያም ከሳሾቹ በአጭሩ ከተዘረዘሩት አንጋፋ ጠበቆች መካከል አንዱን የሚመርጡት እንደ ተጽእኖ የለለበት ገምጋሚ ጠበቃ ሆነው እንዲሾሙ ነው።

(c) አስተዳዳሪው ጉዳዩን ለተስእኖ በሌለበት ገምጋሚ በማመልከት በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ የሚከተሉትን ቁሳቁሶች ለተስእኖ የሌለበት ገምጋሚ ሪከርድን ማቅረብ አለበት።

  (i) የቡድን አባል የአቤቱታ ማስታወቂያ፤

  (ii) የቡድን አባል የመጀመሪያ ማስታወቂያ፤

  (iii) ከቡድን አባል የሚጠየቅ እንደገና ግምገማ እንዲደረግ ጥያቄ እና ማንኛውም ምክንያቶች እና የቡድን አባል ያቀረበውን የድጋፍ ሰነድ፤ እና

  (iv) ለአስተዳዳሪው የቡድን አባል የቀረቡ ሰነዶችን፤

  (v) የቡድን አባል በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል ወይም በቡድን አባል እድሜ ላይ ለመሳተፍ ብቁ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን በአስተዳዳሪው የተያዙና/ወይም የሚታመኑ ሰነዶች።

(d) ከአስተዳዳሪው የሰነድ ቁሳቁሶቹን በተቀበሉ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ፣ ተጽእኖ በለለበት ግምገማ አስተያየት ሰጪው ውሳኔ ስር የአስተዳዳሪውን ውሳኔ ለማረጋገጥ ወይም ለማሻሻል መወሰን አለበት (**ተጽእኖ በለለበት ገምጋሚ የቀረበ ውሳኔ**) እና ለአስተዳዳሪው በነጻ አስተያየት ሰጪ ውሳኔ ምክንያቶችን አጠር ያለ ጽሁፋዊ መግለጫ ማቅረብ ያለበት፤

(e) ከአስተዳዳሪው በኋላ ወይም፡-

  (i) የመጀመሪያ ማስታወቂያ ውስጥ የመጀመሪያውን ውሳኔ ከተስተካከለበት፤ ወይም

  (ii) የገለልተኛ ገምጋሚን ውሳኔ ይቀበላል፣

  አስተዳዳሪው በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ለቡድን አባል "**የግምገማ ክለሳ ማስታወቂያ**" ይልካል። በዚህ ምክኒያት አስተዳዳሪው የግምገማውን ውጤት ለቡድን አባል ያሳውቃል፤ እንዲሁም

(f) አስተዳዳሪው የክለሳውን ውጤት ለማንጸባረቅ የቡድን አባላት መዝገብ ማሻሻያ ማድረግ አለበት።

## 6.5 በገለልተኛ ነጻ ውሳኔ የመጨረሻ እና አስገዳጅ ነው።

የገለልተኛ ነጻ ውሳኔ በአስተዳዳሪው እና ክለሳውን በፈለጉት የቡድን አባል ላይ የመጨረሻ እና አስገዳጅ ነው።

# 7 ለአቤቱታ ባር

አንድ የቡድን አባል በአንቀጽ ህግ 5(ሀ)(iii) በሚለው አንቀጽ 6.2 እና/ወይም አንቀጽ ህግ 6.4 ላይ የተጠቀሱት ንኡስ አንቀጾች ላይ የተጠቀሱትን ማስታወቂያዎች መልስ ለአስተዳዳሪው የማያቀርብ ከሆነ ከነዚህ ድንጋጌዎች ጋር በተያያዘ የቡድን

አባል ተጨማሪ ጥያቄ እንዳያቀርብ ይከለከላል።

# 8 እያንዳንዱ ብቃት ያለው የቡድን አባል ክፍያዎች ስሌት

በአንቀጽ ህግ 6 ላይ ያለው የግምገማ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ ተግባራዊ ሊሆን እንደቻለ አስተዳዳሪው ማሳወቅ ያለበት:

(a) እያንዳንዱ ብቃት ያለው ቡድን አባል ክፍያ የሚከተለውን ዘዴ በመጠቀም መጠኑ ይሰላል:

(i) የመክፈያ ገንዘብ ከመፍትሄ ማስገኛ መጠን ውሰጥ ላይ ይቀነሳል፤

(ii) አስተዳዳሪው በሚከተለው መልኩ በዕርዳታ ውሂብ ስርጭት ላይ ለመሳተፍ ለተመዘገበ ለእያንዳንዱ ብቃት ያለው ቡድን አባል ዩኒቶችን ይመድባል:

(A) እያንዳንዱ የሚፈቀድለት አዋቂዎች ብቃት ያለው ቡድን አባል - 2 ክፍል/ዩኒት

(B) እያንዳንዱ የሚፈቀድለት ህጻናት ብቃት ያለው ቡድን አባል - 1 ክፍል/ዩኒት

(iii) አስተዳዳሪው የቡድን አባል ክፍሎች ያለውን ጠቅላላ ቁጥር ያሰላል፤ እንዲሁም

(iv) አስተዳዳሪው የሚከተሉትን ቀመሮች በመጠቀም እያንዳንዱን ብቁ የቡድን አባል ክፍያን ያሰላል:

$$Adult\ Eligible\ Group\ Member\ Payment\ = 2x\ \frac{(Settlement\ Sum - Reimbursement\ Amounts)}{Total\ Number\ of\ Units}$$

$$Child\ Eligible\ Group\ Member\ Payment\ = 1x\ \frac{(Settlement\ Sum - Reimbursement\ Amounts)}{Total\ Number\ of\ Units}$$

# 9 እንደገና ግምገማ ላይ ማሳሰቢያ

አስተዳዳሪው ከላይ ባለው አንቀጽ ህግ 8 መሰረት ሁሉንም ብቃት ያላቸው የቡድን አባል ክፍያዎች ስሌት ከተካሄደ በኋላ አስተዳዳሪው ወዲያውኑ ለእያንዳንዱ ብቁ ቡድን አባል ለሆነ የቡድን አባልክፍያን ከመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ እንዲቀርብ የግምገማ ማስታወቂያ ይልካል።

# 10 ከመፍትሄ ማስገኛ መጠን ውሰጥ የሚከፈል ክፍያ

## 10.1 የከሳሾች ተመላሽ ክፍያ

በ20 የሥራ ቀናት ውስጥ በስምምነት ትእዛዞች ቀን ላይ አስተዳዳሪው ከስምምነት ገንዘብ ለእያንዳንዱ ተከሳሽ የመልሶ ማከፋፈያ ገንዘብ መክፈል አለበት።

## 10.2 የቡድን አባል ክፍያዎች

በ60 የሥራ ቀናት ውስጥ:

(a) የመጨረሻው ገለልተኛ ገምጋሚ ውሳኔ ወጥቷል፤ ወይም

(b) በመጨረሻ የመጀመሪያ ማሳሰቢያ እንደሚወጣ፤ የትኛውም የቡድን አባል ግምገማ ከለሳ

እንደሚፈልግ ታዲያ አስተዳዳሪው የቡድን አባል ክፍያዎች ማከፋፈል አለበት።

# 11 የመፍትሄ ማስገኛ ክፍያ ማሳሰቢያ

የግምገማ ክለሳ አሰራር ሂደቱ ከተጠናቀቀ እና አስተዳዳሪው ከላይ በአንቀጽ ህግ 8 መሰረት ሁሉንም ብቃት ያለው ቡድን አባል ክፍያዎችን ካሰላ በኋላ አስተዳዳሪው ወዲያውኑ ለእያንዳንዱ ብቁ ቡድን አባል ማካተት ያለበትን የመፍትሄ ማስገኛ ክፍያ ማስታወቂያ እንደሚላክ: በዚህ የሚከተሉትን መረጃዎች ያካትታል:

(a) የቡድን አባል የክፍያ መጠን፤

(b) የአስተዳዳሪው የብቃት ቡድን አባል የመፍትሄ ማስገኛ መጠን ስሌት ዝርዝር፤ እና

(c) የመፍትሄ ማስገኛ ክፍያ የገባበት የብቃት ቡድን አባል የባንክ አካውንት ዝርዝር።

# 12 ማሳሰቢያዎች

(a) በዚህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር መሰረት ሊሰጥ የሚገባው ማንኛውም ማሳሰቢያ ወይም የሃሳብ ልውውጥ ከዚህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር ጋር ለተያያዙ ለሁሉም ዓላማዎች የተሰጠና የሚቀበል ከሆነ፡

(i) ለተሰጠው ሰው የተላከበት፤

(ii) ወይም፡-

(A) በቡድን አባላት መመዝገቢያ/ሬጅስትራር ላይ የተመዘገበውን የዚያን ሰው የኢሜይል አድራሻ በኢሜይል በመላክ "ያልተላከ" መልስ ለላኪው አይደርስም፤ ወይም

(B) በቅድሚያ ክፍያ የተከፈለበት ኤንቨሎፕ ደብዳቤ፣ በቡድን አባላት መዝገብ ሬጂስትር ላይ የኢሜይል አድራሻ ወደሌለበት ወደ ግለሰቡ የፖስታ አድራሻ ይላካል።

(b) ከዚህ አንቀጽ ህግ ጋር የሚታዘዝ ማንኛውም ማስታወቂያ ወይም የሀሳብ ልውውጥ መስጫና መቀበያ ተደርጎ ይቆጠራል፡

(i) በተላከበት ጊዜ፤ በኢሜይል ቢላክም፤

(ii) በአውስትራሊያ ወደ ተፈለገ አድራሻ በፖስታ የተላከ ከሆነ፣ ከተላከ በኋላ ሶስት ግልጽ የሥራ ቀናት፤ ወይም

(iii) ወደ ውጭ አገር አድራሻ በፖስታ የተላከ ከሆነ፤ በተላከበት ከአምስት ግልጽ የሥራ ቀናት በኋላ ይደርሳል።

(c) አስተዳዳሪው ለላኪው ሌላ ነገር ካላሳወቀና እስካልነገረ ድረስ የአስተዳዳሪው አድራሻ ዝርዝር እንደሚከተለው ይሆናል፡

በደብዳቤ አድራሻ 50 Lonsdale St, Melbourne Victoria

3000

በኢሜይል COVID-19-Towers@health.vic.gov.au

# 13 የሚወስደው ጊዜ

(a) አስተዳዳሪው ይህን የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት ስርዓት አስተዳደር ከስምምነት ትእዛዞች ከተደረገበት ቀን በ180 ቀናት ውስጥ ለማጠናቀቅ ጥረት ማድረግ አለበት።

(b) በሌላ ትእዛዝ ከተሰጠበት ካልሆነ በስተቀር አስተዳዳሪው በዚህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር ሥር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ጊዜ ወይም ሰዓት ሊወስን ይችላል። የመርሃ ግብሩ ዓላማን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል።

(c) በፍርድ ቤቱ የተሰጠ ማንኛውም ትእዛዝ መሰረት ማንኛውም ድርጊት ለመፈጸም ወይም በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ማከፋፈያ መርሃ ግብር ስር የሚከናወነው ጊዜ በአስተዳዳሪው ፍጹም በሆነ ጥንቃቄ ሊራዘም ይችላል።

(d) ማንኛውም ድርጊት ወይም በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ማከፋፈያ መርሃ ግብር መሰረት የሚካሄድበት ጊዜ በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሊራዘም ወይም ሊታለፍ ይችላል።

# 14 አስተዳደር ስለመጠናቀቅ

## 14.1 የገንዘብ ስርጭት ሪፖርት

(a) የመጨረሻው የቡድን አባል ክፍያ ከመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ የሚከፋፈልበትን ቀን ተከትሎ በ20 የሥራ ቀናት ውስጥ አስተዳዳሪው ለፍርድ ቤቱ አጭር ሪፖርት ማቅረብ ያለበት፡

(i) ለእያንዳንዱ ብቁ ቡድን አባላት የተከፈለውን ጠቅላላ ገንዘብ፤ እና

(ii) ከመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ መጠን ውስጥ ክፍያን የተቀበሉ የቡድን አባላት ቁጥር።

(b) አስተዳዳሪው በአንቀጽ ህግ ቁጥር 14.1(ሀ) ላይ የተገለጸውን ሪፖርት ለፍርድ ቤቱ ከተሰጠ በኋላ ተግባራዊ ሊሆን እንደቻለ በስርጭት አካውንት ውስጥ ያሉት ሁሉም ገንዘቦች በመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት መርሃ ግብር፣ በመርሃ ግብር እና በፍርድ ቤቱ በተሰጠው ማናቸውም ትእዛዝ መሰረት ተደርጎ የተከፋፈለ መሆኑን

ለከሳሽ እና ለተከሳሽ ህጋዊ ተወካዮች ማሳወቅ አለበት።

### 14.2 የአስተዳደር መጨረሻ

ፍርድ ቤቱ ሌላ ትእዛዝ ካልተሰጠ በስተቀር አስተዳዳሪው በሚከተሉት መጨረሻ ጊዜ ላይ አስተዳዳሪነቱን ማቆም አለበት

(a) ሁሉንም የመፍትሄ ማስገኛ ክፍያዎች ለብቁ ፈቃድ ላላቸው ቡድን አባላት ማከፋፈል እንደተቻለ፤

(b) በአንቀጽ ህግ 10 0 መሰረት የሚከፈል ገንዘብ ላጠናቀቀ፤

(c) የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ መጠን ተሟጦ ያለቀ፤ ወይም

(d) ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ ህግ 14.1 ሥር ሪፖርት ማቅረብ።

## 15 አተረጓጎም

በጥቅሱ ዙሪያ ያለው ሀሳብ ከሌላ ካላስፈለገ በስተቀር የሚከተሉት ደንቦች ይሰራሉ፡

(a) ርዕሰ አንቀጾችና ስመ ቅደም ተከተሎች ለምቾት ብቻ የሚጠቅሙ ከመሆናቸውም በላይ በትርጉም ላይ ተጽዕኖ አያሳድሩም።

(b) ይህ ነጠላ ቃል ብዙ ቁጥርን የሚጨምር ሲሆን መቀያየሩም ይሠራል ።

(c) አንድ ፆታ ሁሉንም ፆታዎች ያካትታል።

(d) አንድ ቃል ወይም ሀረግ ከተገለጸ ሌሎቹ የሰዋስው አጻጻፎችም ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው።

(e) አንድን ሰው ወደ ሚመለከተው መላክ በአንድ ድርጅት፣ መተማመንን፤ ኢጋርነትን፣ ያልተካተተ አካል ወይም ሌላ ለየት ያለ ህጋዊ ሙብት ያለውን አካል ያካትታል።

(f) ወደ ዶላርና $ የሚጠቅሰው የአውስትራሊያ ገንዘብን ነው።

(g) በማንኛውም ሰው የሚደረግ ማንኛውንም ነገር ወደሚመለከተው መላኩ በዳይሬክተር፣ በሀላፊ፣ በአገልጋይ፣ በወኪል፣ በግል ተወካይ ወይም በህግ ተወካይነት በህግ ወይም በማናቸውም የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስምምነት ወይም በዚህ የመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል መርሃ ግብር እንዲፈቀድለት የተፈቀደውን ነገር መጥቀስን ያካትታል።